የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.11
ADDIS ABABA 13th January, 2017

አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፰/፪ሺ፱ ዓ.ም

ከቃሊቲ - ቀለበት መንገድ አደባባይ እስከ ቱሉ ዲምቱ አደባባይ መንገድ እንዲሁም ከቃሊቲ ቀለበት መንገድ፣ በቡልቡላ እስከ ቂሊንጦ አደባባይ መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ገጽ..... ........................................................፱ሺ፭፻፯

Proclamation No. 988/2017

Export – Import Bank of China Loan Agreement for financing Kality Ring Road Interchange Tulu Dimtu Roundabout Road and Kality Ring Road Bulbula - Kilinto Roundabout Road Projects Ratification Proclamation................…. --Page 9507

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፰/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ <u>የወጣ አዋጅ</u>

ከቃሊቲ - ቀለበት መንገድ አደባባይ እስከ ቱሉ ዲምቱ አደባባይ መንገድ እንዲሁም ከቃሊቲ ቀለበት መንገድ ፣ በቡልቡላ እስከ ቂሊንጦ አደባባይ መንገድ ፕሮጀክት ከፊል ማሰፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፪ ሚሊዮን ፯፻፴፮ ሺ ፩፻፵፯.፶፫ የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሰባት ከሃምሳ ሦስት ሣንቲም) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፬ ቀን ፪ሺ፲፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን የበድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 988/2017.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOANAGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA <u>AND EXPORT- IMPORT BANK OF CHINA</u>

WHEREAS, a loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Export- Import Bank of China stipulating that the Export – Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia Loan in amount equivalent to one hundred two million seven hundred thirty six thousand one hundred forty seven and fifty three cents (102,736,147.53 USD) for financing Kality Ring Road Interchange Tulu Dimtu Roundabout Road and Kality Ring Road Bulbula - Kilinto Roundabout Road Project was signed in Addis Ababa on the 4th day of October 2016;

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 27th day of December, 2016;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከቃሊቲ - ቀለበት መንገድ አደባባይ እስከ ቱሉ ዲምቱ አደባባይ መንገድ እንዲሁም ከቃሊቲ ቀለበት መንገድ ፣ በቡልቡላ እስከ ቂሊንጦ አደባባይ መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከቻይና ኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፰/፪ሺ፱ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፬ ቀን ፪ሺ፲፮ በአዲስ አበባ የተፈረመው ውል ቁጥር BLAETH 2016001 የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምመነቱ የተገኘውን ፩፻፪ ሚሊዮን ፯፻፴፮ ሺ ፩፻፵፯.፶፫ የአሜሪካን ዶላር (አንድ መቶ ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሰባት ከሃምሳ ሦስት ሣንቲም) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export – Import Bank of China Loan Agreement for financing Kality Ring Road Interchange Tulu Dimtu Roundabout Road and Kality Ring Road Bulbula - Kilinto Roundabout Road Projects Ratification Proclamation No. 988/2017".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement Contract No. BLAETH2016001 signed in Addis Ababa on October 04th 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Export- Import Bank of China is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of one hundred two million seven hundred thirty six thousand one hundred forty seven and fifty three cents (102,736,147.53 USD) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall in to force on the date its publication in the Federal Gazette.

Done at Addis Ababa, this 13th day of January, 2017

**Dr. MULATU TESHOME**

**PRESIDANT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**